# በክረምት በዓላት ወቅት የሚከሰቱ እሳቶች ይከላከሉ

በዊንተር ወቅት የሚከበሩ በዓላትን አስመልክቶ ቤትን ማስዋብ አስደሳች ነገር ነው፣ ነገር ግን የበዓል ማስጌጫዎች በእቤት ውስጥ ለሚከሰት የእሳት አደጋ ሊያጋልጡ ይችላሉ። ቤትዎን በሚያስጌጡበት በዚህ ወቅት ጥንቃቄ ያድርጉ።

- በዲሴምበር ወር ውስጥ በቤት ማስጌጫ ምክኒያት ከተከሰቱት የእሳት አደጋዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በሻማዎች ምክኒያት የተከሰቱ ናቸው።
- ከ 1/3 በላይ በቤት ማስጌጫ ምክኒያት የሚነሱ የእሳት አደጋዎች በሻማ ምክኒያት የሚከሰቱ ናቸው።
- በሻማ ምክኒያት የሚነሱ እሳቶች የሚከሰቱባቸው ከፍተኛዎቹ 3 ቀናት የገና ቀን፣ የአዲስ ዓመት ቀን እና የአዲስ ዓመት ዋዜማ ናቸው።
- ሻማዎችን ከማንኛውም ሊቀጣጠል ከሚችል ነገር ቢያንስ 12 ኢንች ያህል ያርቁ።
- ምንም እንኳን በገና ዛፍ ምክኒያት የሚነሱ እሳቶች የተለመዱ ባይሆኑም፣ ከተከሰቱ ግን በጣም አደገኛ ናቸው።

  በአማካኝ ሪፖርት ከተደረጉ 52 በገና ዛፍ ምክኒያት የሚነሱ የእሳት አደጋዎች መካከል አንዱ የሞት አደጋን ያደረሰ ነው።
- ከ 4 ቱ በዊንተር ወቅት ከሚከሰቱ የእሳት አደጋዎች ውስጥ አንዱ ለገና ዛፍ በጣም ቅርብ በሆነ የቤት ማሞቂያ መሳሪያ ምክኒያት የሚከሰት ነው።
- ምን ያህል የማስጌጫ መብራቶችን መጠቀም እንዳለብዎት በትክክል ለማወቅ የአምራቹን መመሪያዎችን ያንብቡ።
- እንደ የእሳት ማሞቂያዎች፣ ራዲያተሮች፣ የቤት ማሞቂያዎች፣ ሻማዎች ወይም የሙቀት ማውጫዎች ካልዎት ያስቀመጡት የገና ዛፍ ቢያንስ በ 3 ጫማ ርቀት ላይ መሆኑን ያረጋግጡ። በተጨማሪም፣ ያሎት የገና ዛፉ መውጫ በሮችን እንደማይዘጋ እርግጠኛ ይሁኑ።
- ከገና በአል በኋላ ወይም በሚደርቅበት ጊዜ የገና ዛፍዎን ያስወግዱ።

ለነጻ የቤት ደህንነት ፍተሻ ወደ 311 ይደውሉ፣ www.mcfrs.org/mcsafe